# የውርግርግ ፏፏቴ

በምስራቅ ጎጃም ዞን በሁለት እጁ እነሴ፣በባሶሊበን እና በእናርጅ እናዉጋ ወረዳዎች ዉርግርግ በሚል ስያሜየሚጠሩ ፏፏቴዎች አሉ፡፡ ዛሬ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ የሚገኘዉን ዉርግርግ ፏፏቴ እናስተዋዉቃችኋለን፡፡ ከሞጣ ከተማ ተነስተን 5 ኪ.ሜ በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኘውን የህብረ ሰላም ቀበሌ የተንጣለለ ጥቁር አፈር አቋርጠን 1፡ 00 ሰዓት የእግር ጉዞ ካደረግን በኋላ በህብረ ሰላም ቀበሌ እና በገዳም አቦ ቀበሌ መካከል በሰዴ ወንዝ ላይ **የውርግርግ ፏፏቴን** የተፈጥሮ የመስህብ ሃብት እናገኛለን፡፡የውርግርግ ፏፏቴ በስተምዕራብ የሴሞፋፏቴ፤በስተምስራቅ በገዳምአቦ ቀበሌ የተፈጥሮ ደን እንዲሁም በስተደቡብ ረግረጋማ ቦታዎች መገኘታቸዉ ልዩ ግርማ ሞገስን አጎናጽፎታል፡፡

የውርግርግ ፏፏቴ ውርግርግ የሚለውን ስያሜ ያገኘው በአካባቢው ረግረጋማቦታ ስለነበር ረግረግ ከሚለውቃል እንደተወሰደ ይነገራል፡፡

ውርግርግ ሶስት ፏፏቴዎች አሉት፡፡ አንደኛው ክረምት እስከ በጋ የመንገድ አገልግሎት የሚሰጥ ፏፏቴ ሲሆን ሁለተኛው ከዋናው ወረድ ብሎ ውሃው ወደ ጉሬ ውስጥ የሚገባበት ቦታ የሚገኝ ፏፏቴ ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ውሃው በበርሃው ቀጥታ በሚገባበት ጊዜ የሚፈጠረው ፏፏቴና በክረምት ወራት ቀስተ ዳመና የሚተክል ፏፏቴ ነው፡፡

እነዚህ ሶስቱም ፏፏቴዎች ህብረት በመፍጠር እና በዙሪያው በሚገኙ ሌሎች መስህቦች በመታጀብ የቱሪስትን ልብ ያማልላሉ፡፡ በዚህ ጽሁፍ

የምናየው የመጀመሪያውንና ዋናውን የፏፏቴ ክፍል የሆነውንና ለመሸጋገሪያነት የሚያገለግል ፏፏቴ ይሆናል፡፡

የውርግርግ ፏፏቴ በደን የተሸፈነ ስለነበረ ለዘመናት የአካባቢው ህ/ሰብ ሳያውቀው የነበረና የአንድ ግለሰብ ሀብት የነበረች ላም በሬዎችን አስከትላ በጫካው ገበታ እንደጠፋችና ከ2 ቀን ቆይታ በኋላ ባለቤቷ የገባችበትን ጣሻ ተከትሎ በመግባት ላሟ ውርግርግ ዋሻ ውስጥ ተጠልላ እንዳገኛት እንዲሁም በዋሻው ውስጥ ውሃ ሳያገኘው ይዟት ተሻግሮ በጫካው ያለውን ድንቅ ዋሻና ፏፏቴ ለአካባቢው ህ/ሰብ በማስተዋወቅና ጫካውን በመመንጠር ዋሻውለመሸጋገሪያነት/ለመንገድ/ አገልግሎት መስጠት እንደጀመረ በአፈታሪክ ይነገራል፡፡

ይህ ፏፏቴ ከሚወርድበትና ከሚያርፍበት ቦታ በስተውስጥ በኩል በግምት 6 ሜትር ርዝመት እንዲሁም ውሃው ከሚወርድበት ከላይ ወደታች 10 ሜትር ከፍታ ያለው ልዩ መግነጢሳዊ ሃይል ያለው ድንቅ ዋሻ እና የተፈጥሮ ደን ፏፏቴውን ግርማ ሞገስ አጎናጽፎታል፡፡ ሌላውና ፏፏቴውን ልዩ የተፈጥሮ ገጸ በረከት ከሚያስኙት ጉዳዮች መካከል በዋሻው ውስጥ ሙሉ በጋና ክረምት ሰዎች ዋሻውን እንደመሸጋገሪያ ድልድይ መጠቀምመቻላቸውነው፡፡

የፏፏቴው የውሃ መጠን እንደየወቅቱ ሁኔታ በበጋና በክረምት የሚለያይ ቢሆንምየሃገር ውስጥምሆነ የውጭ ሃገር ቱሪስቶችን ቀልብ መሳብና ማማለል የሚችል የተፈጥሮ የመስህብ ሃብት ነው፡፡

የውርግርግ ፏፏቴ በመሀተምድንግል ዋሻ እና በሴሞፏፏቴ በመታጀብ የበርካታ ቱሪስቶችን ልብ በማሸፈት የተፈጥሮን ድንቅ ስራ በአረምሞ

በማሳየት የአካባቢውህ/ሰብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል የተፈጥሮ የመስህብ ሃብት ነው፡ ፡

የውርግርግ ፏፏቴ የብዝሀ ህይወት መገኛ እንደነበር አፈታሪኮች ያስረዳሉ፡ ፡ በአካባቢው ከሚገኙ የእጽዋት ዝርያዎች መካከልም ሸነት፣ አጋም፣ ገተም፣ ናጩ፣ እና ሌሎችም ሃገር በቀል ዛፎች እንደነበሩና በውስጡም የዱር እንስሳትና የአእዋፍት ዝርያዎች እንደ ጅብ፣ ድኩላ፣ ሰሳ፣ አሳማና ሌሎች ይገኙበት/ይጠለሉበት/እንደነበር አፈታሪኮች ያስረዳሉ፡ ፡

በአሁኑ ጊዜ የውርግርግ ፏፏቴን የሚሸፍነው አካባቢ ለልቅ ግጦሽና ለእርሻ አገልግሎት ከመዋሉ የተነሳ የስነ ምህዳራዊ ተጽዕኖ እየደረሰበትና የረግረጋማ ቦታዎች የመድረቅ ፣ደኖች የመመናመንና የመጥፋት አደጋ እየደረሰባቸውይገኛል፡ ፡

በመሆኑም የአካባቢው ህብረተሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጀቶችና ግለሰቦች የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት በማልማት፣ ስነ



ምህዳራዊ ይዘቱን በማስጠበቅና በመንከባከብ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮችን በመዘርጋት ለቱሪስቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና ለኢኮኖሚው እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስቻል ይገባል እያልን የውርግርግ ፏፏቴን ይጐብኙ ፣ይወቁ እና ያስተዋውቁ መልዕክታችን ነው፡ ፡

# ሰባራው የአባይ ድልድይ

መነሻችን ከሞጣ ከተማ ሆኖ እስቴን በአሻጋሪ እያየን አባይን ለማቋረጥ በምናደርገው ጉዞ የማያጋጥመን ታሪካዊ ድልድይ ነው፡ ፡ በ1630 ዎቹ አካባቢ በንጉስ ፋሲለደስ ዘመነ መንግስት የድልድይ ስራ እንቅስቃሴ በጉልህ የታየበት ወቅት ነበር፡ ፡ ከነዚህ የድልድይ ስራ ተግባሮች መካከል በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ የጐንደር እስቴ መገናኛ ላይ የተሰራው ድልድይ አንዱ ነው፡ ፡ ይህ ድልድይ ከሞጣ ከተማ በስተሰሜን 22 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡ ፡ ድልድዩ አራት ሜትር ከፍታና 60 ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን በወቅቱ የድልድዩ መሰራት ዓላማም በወቅቱ አጠራር የጐጃምን ክፍለ ከጐንደር ክፍለ ሃገር ጋር ለማገናኘት ነበር፡ ፡ የዚህ ድልድይ ግንባታ ከጅምሩ አያሌ ኢትዮጰያውያን የተረባረቡበት እና ያለ ሃላቸውን የጨረሱበት እንደሆነ ሲታወቅ የፖርቱጋል ባለሙያዎች እጅም እንዳለበት በአፈ-ታሪክ ይነገራል፡ ፡ የአክሱምን ሃውልትና የላሊበላን ዉቅር አብያተ ክርስቲያናት የሰሩ የኢትዮጵያ ስነ-ህንጻ ባለሙያዎች ይህንን ድልድይ በመስራትምረቂቅ ጥበበኞች መሆናቸዉን ዳግምአሳይተዋል፡ ፡

ይህ ድልድዩ ተገንብቶ ለ300/ሶስት መቶ/ አመታት ያህል አገልግሎት የሰጠና በተለያዩ ጊዜያት ጥገናና እድሳት ሲደረግለትምቆይቷል፡ ፡ የድልድዩ መሰበር መሰረታዊ መነሻውኢጣልያ ሃገራችንን በወረረችበት ወቅት በ1928 ዓ.ም የጠላት ወገን ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር እንዳይሻገር ለመከላከል ሲባል እንደነበር ይነገራል፡ ፡

**ድልድዩን ማን አፈረሰው**

ከታሪክ ለመገንዘብ እንደሚቻለው አውሮፖውያን አፍሪካን ለመቀራመት የድርሻ ስምሪት በደረጉበት የወረራ ዘመን ኢትዮጵያምከተወራሪዎች አንዷ ነበረች፡ ፡ ኢጣሊያ ከአድዋ ጦርነት ሽንፈት ማግስት በ1928 ዓ.ም የጦር ሀይሏን በዘመናዊ መሳሪያ አስታጥቃና ታጅባ እራሷን እነደገና በማጠናከርና በማደራጀት ኢትዮጵያን ለመቀራመት ወረራ አደረገች፡ ፡ የኢትዮጵያ

አይበገሬ የአርበኞች ህብረት በመፍጠር ትግሉን በፋኖ ተሰማራ መፈክር ሳሩ ዱሩ ቤቴ በማለት ትግሉን ተያያዘው፡፡ በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ወታደር የደፈጣ ውጊያን/ guerrilla fighting/ እንደ አማራጭ ሆነ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሁለት እጁ እነሴ ወረዳ የደፈጣ ውጊያ መሪ የሆኑት ፊታውራሪ ታምራት /አባ ወማቀ ታሜ/ ነበሩ፡፡ ፊታውራሪ ታምራት የተወለዱት ልዩ ስሟ አውሳ በምትባል መንደር ሰረቀ ብረሃን ቀበሌ ሲሆን የሁለት እጁ እነሴና የጐንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ ምስለኔ /ገዥ/ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ፊውታውራሪ ታምራት የኢጣሊያኖችን ጥቃት አጥብቀው ለመከላከል ከነበራቸው ምኞት የተነሳ ወደ ጐጃም ክፍለ ሃገር እንዳይሻገሩ ለማድረግ እንደ አማራጭ የተወሰደው ይህን የአባይ ድልድይ በመስበር ማቋረጥ የሚል ነበር፡፡ 1928 ዓ.ም በነሀሴ ወር አጋማሽ ላይ ፀሐይ በምህዋሯ ጮራዋን ሰንጥቃ ከመውጣቷ በፊት ይህን በጥንካሬ የተሰራ ድልድይ ለማፍረስ ፊታውራሪ ታምራት የሚመሩት የሰው ሃይል በከፍተኛ ደረጃ ማፈረሱን ተያያዘው፡ ይሁን እንጅ የአባይ ወንዝ በመሙላት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ወቅትና ውሃው ግራና ቀኝ መግደል ሰርቶ ይናጥ በነበረበት ጊዜ ዙሪያውን የደለል ክምችት ስለነበር ለማፍረስ ብዙ ውጣ ውረድ ፈጅቷል፡፡ ፊታውራሪና ተከታዮቻቸው የተለያዩ ባህላዊ መሳሪያዎችና መዶሻዎችን በመያዝ የኑግ ዘይት እያረበረቡ ለተከታታይ 23 ቀናት የድልድይ ማፍረሱን ተግባር ተያያዙት፡፡

መስከረም 3/1929 ዓ.ም የሰው ሃይል በማፍረስ ተግባር ላይ እንደተሰማራ ፊታውራሪ ታምራትን ጨምሮ ከጐንደር 16 ሰዎች ከጎጃም 54 ሰዎች በድምሩ 7o የሰው ሃይል እንደተሰማራ ድልድዩ ተደረመሰ፡፡ ያለው የሰው ሃይልም ከውሃ ጋር ተጨመረ፡፡ በዚህ ምክንያት ፊታውራሪ ታምራትና ግብረ አበሮቻቸው ህይወት በአሰቃቂ ሁኔታ የመጨረሻ ፍጻሜ ሆነ፡፡ ከድልድይ ባሻገር የፊታውራሪ ታምራት ልጅ የሆኑት ፊታውራሪ ተሰማ ታምራት በህይወት በመትረፋቸው የሁኔታውን አስደንጋጭነት ወደ ህዝቡ በመሄድ አስረዱ፡፡

የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር በድልድዩ መሰበር ምክንያት ይቀራል ተብሎ የታሰበው የኢጣሊያ ጦር አባይን ተሻግሮ አካባቢውን አጥለቀለቀው፡ የፊታውራሪና የተከታዮቻቸው ወገኖች ሃዘናቸው እጥፍ ድርብ ሆነ፡፡ በዚህም ወቅት ይቀርቡ የነበሩ እንጉርጉሮዎችን ለአብነት ያህል አቅርበናል፡፡

- ዋይ በሉ
- አባ ወማታሜን ወማዋጠውአሉ
- አባ ወማየሚሉት ክፋ የፈረስ ስምድልድዩንና ጌታውን አደረገውድርስም

● አይ አባይ! አይ አባይ ! ድመትን መሳይ የወለድከውን ልጅ ትበላለህ ወይ

● በማለት ብሶታቸውን ይገልፁ ነበር፡፡

በመጨረሻ የዚህ ድልድይ እጣ ፈንታ ለመሸጋገሪያነት ማዶ እና ማዶ ገመድ በመወጠር በሰዎች ጉልበት ወገቡን የታሰረ ተጓጓዥ ወደ ተፈለገውአቅጣጫስለ ማሻገር ተጀመረ፡፡

ስሙም ሰባራው ድልድይ ተባለ

በዚህ የመሸጋገር ስልት ወቅት ታስሮ የሚጓጓዘውን ወገን ክፍያ ለማስጨመር ሰርበው፣ አቃናው፣ አጠጣው እየተባለ መሃል ወንዝ ላይ ኑዛዜውን ይጨርስ እንደነበር ይነገራል፡፡ በኋላም የህዝቡን ስቃይ የተመለከቱ በጎ አድራጊዎች ከቀድሞዉ ድልድይ ጐን በሸቦና በጣውላ ርብራብ ሌላ ድልድይ እንዲሰራ በማድረጋቸዉ የነበረው የገመድ መጓጓዣ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

ጊዜ አይፈታዉ ነገር የለምና ይህ ሁሉ ችግር አልፎ በአሁኑ ሰዓት ምስራቅ ጎጃምን እና ደቡብ ጎንደርን የሚያገናኝ መንገድ በመገንባት ላይ በመሆኑ ሁለቱን ዞኖች ከማገናኘትና ህዝቡን ከማገናኘት አልፎ ይህንን ታሪካዊ ድልድይም ወደ ቱሪዝም ገባያ ለማስገባት ምቹ አጋጣሚ ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

